በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቀን ጥቅምት 21 2012
Date
ቁጥር 4/0266/12
Ref.No.

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የተሻሻለውን የጉምሩክ አዋጅ 1160/2011 ዓ.ም ስለመላክ፤</u>

የተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ 1160/2011 ዓ.ም ፀድቆ እና ታትሞ የደረሰን መሆኑን እየገለፅን፤ በዚሁ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አዋጁንና ለውጥ የተደረገባቸውን አንቀፆች የሚያሳይ 17 ገፅ መግለጫ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልፃለን::

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

24/02/2012

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☎ +251 116 62 98 00
+251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

- ለአ/አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)
- ለአ/አ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት(2)

  <u>አዲስ አበባ</u>

- ለአዳማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>አዳማ</u>

- ለአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>አዋሽ</u>

- ለባህር ዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ባህር ዳር</u>

- ለኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ኮምቦልቻ</u>

- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ድሬዳዋ</u>

- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ጋላፊ</u>

- ለሐዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ሐዋሳ</u>

- ለጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ጅግጅጋ</u>

- ለጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ጅማ</u>

- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>መቀሌ</u>

- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ሞጆ</u>

- ለሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት (2)

  <u>ሞያሌ</u>

| ተ/ቁ | የተሻሻሉ አንቀጾች | የነበረው ድንጋጌ | አዲሱ ድንጋጌ | የተሻሻለበት ምክንያት |
|---|---|---|---|---|
| 01 (ትርጉም) | አንቀጽ 2 (49) | "በሕጋዊ ዕቃ ከለላነት መጠቀም" ማለት የጉምሩክ ድክለራሲዮን ከቀረበበት ዕቃ ጋር በዓይነት፣ በመጠን፣ በብዛት፣ በዋጋ ወይም በስሪት አገር ልዩነት ያለውን ዕቃ የመቀላቀል ደርጊት ነው፡፡ | "በሕጋዊ ዕቃ ከለላነት መጠቀም" ማለት የዕቃ ዲክላሪሲዮን ከቀረበበት ህጋዊ ዕቃ ጋር የዓይነት፣ የመጠን፣ የመለኪያ፣ የጥራት፣ የብዛት፣ የአገላለጽ እና የስሪት አገር ልዩነት ያለውን ወይም በዲክለራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ዕቃ ቀላቅሎ ወደ አገር ውስጥ የማስገባት ወይም ከአገር የማስወጣት ድርጊት ነው፡፡ | • ንዑስ አንቀጹ ዋጋን በልዩነት ትርጉም ውስጥ ያካተተ በመሆኑና በተግባር ግን አብዛኛው ዕቃ ላይ የዋጋ ልዩነት የሚገኝ በመሆኑ እንደ ልዩነት ተቆጥሮ በአስተዳደራዊ ውሳኔም ሆነ በወንጀል የሚጠየቁበት አግባብ ባለመኖሩ ቃሉን ከትርጓሜ ማውጣት በማስፈለጉ፣<br>• ለልዩነት የተሰጠው ትርጉምም ሙሉና ግልፅ ባለመሆኑ ሁለት ጊዜ ማብራሪያ የተሰጠበት በመሆኑ ያለውን ብዥታ ማጥራት በማስፈለጉ፤<br>• ልዩነት ተብለው በተግባር በየዕለቱ የሚያጋጥሙ ልዩነቶችም በትርጉሙ እንዲካተቱ |
| | (52) | የግል መልገያ ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ በሚስቴሩ መመሪያ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ሆኖ መንገደኛ የሚይዘው ዕቃ ነው፡፡ | "የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ" ማለት ጠቅላላ ዋጋው ወይም ብዛቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ ሆኖ መንገደኛው የሚይዘው ዕቃ ነው፡፡ | |
| | (54) | | "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡ | የገቢዎች ሚኒስቴር አዲስ መሆኑና የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒሳቴርን ወይም የገቢዎች ባላስልጣኑን የነበረውን ለመተካት አዲስ የገባ |
| | (55) | | "ኮሚሽን ወይም ኮሚሽነር" ማለት የጉከሩክ ኮሚሽን ውም ኮሚሽነር ነው፡፡ | የጉምሩክ ኮሚሽን አዲስ መሆኑና እንደ ሁኔታው የገቢዎች ባላስልጣን የነበረውን ለመተካት አዲስ የገባ |
| 02 | አንቀጽ 10(7) የዕቃ | | በአንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም የጉምሩክ ስነ ስርዓት ለመፈፀም አስፈላጊ ከሆኑት አባሪ ሰነዶች መካከል የተወሰኑትን ማቅረብ በማይቻልበት ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ሰነዶቹ ሳይቀርቡ የጉምሩክ ሥነ ስርዓት | ውጭ አገር ኖረው ወደ አገራቸው ለሚመጡ ዜጎች ንብረት የስራት ሀገር የተላያዩ ሰነዶችን ለማቅረብ |

Customs Commission

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 06 | አንቀጽ 21(4) | | ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌ ቢኖርም በትልልቅ ኩባንያዎች ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ በአስመጪው መጋዘን ወይም የሥራ ቦታ ትራንዚት እንዲጠናቀቅበት ኮሚሽኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ | • ከጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያ ውጪ ትራንዚት እንዲጠናቀቅ ለመፍቀድ፤ በዝቅተኛና መካከለኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ ዕቃዎች የውጭ ፍተሻ ሲፈቀድላቸው የጉምሩክ ትራንዚት ኢንስፔክተርን ሳይጠብቁ ትራንዚት እንዲያጠናቅቁ ለመፍቀድ፣ |
| | (5) | | የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ጉምሩክ መዳረሻ ጣቢያ መግባት ሳያስፈልገው በድርጅቱ መጋዘን ወይም የስራ ቦታ ትራንዚት እንዲያጠናቅቅ የተፈቀደለት አስመጪ የዕቃ መልቀቂያ ሳይሰጠው እሽጉን መነካካት፣ መፍታት ወይም ዕቃ ማራገፍ አይችልም፡፡ | አዲስ |
| 07 | አንቀጽ 25(2) | ባለሥልጣኑ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አስመጪው በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመክፈል ዋስትና ሰጥቶ እንዲለቀቁ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሆኖም በዚህ አይነት ለቀረጥና ታክስ ክፍያ የሚሰጠው ጊዜ ከ12 ወራት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡ | ሚኒስቴሩ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት ኮሚሽኑ ለቀረጥና ታክስ ክፍያ ዋስትና በመቀበል ዕቃ ሊለቅ ይችላል፡፡ ሆኖም ቀረጥና ታክሱን ለመክፈል የሚሰጠዉ ጊዜ ከአስራ ሁለት ወራት ሊበልጥ አይችልም፡፡ | • ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ኮሚሽኑ እቃዎችን በዋስትና እንዲለቅ ለማድረግ፣(ባለስልጣኑበኮሞሥኑ፣ ገንዘብ ሚኒስቴር በገቢዎች ሚኒስቴር መተካቱ) |
| 08 | አንቀጽ 26(3) | | የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ(1) ድንጋጌ ቢኖርም ወደ አገር ውስጥ የገባውን ዕቃ ባህሪ መሠረት በማድረግ ኮሚሽኑ በምትከነት የሚገቡ ዕቃዎችን የጊዜ ገደብ ሊያራዝም ይችላል፡፡ ሆኖም የሚራዘመው ጊዜ የዕቃው ላኪ ከተሰጠው የዋስትና ጊዜ ሊበልጥ አይችልም | • ኮሚሽኑ የተበላሹ ዕቃዎችን ተረክቦ የሚያደርገው ነገር በላመኖሩ አስመጪው ዕቃውን ለጉምሩክ አምጥቶ እንዲያስረክብ ማስገደድ አግባብነት ስለማይኖረው እንዲሻሻል ተደርጓል |
| 09 | አንቀጽ 32 | | 3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው በካርጎ ወይም በየብስ ማጓጓዣ የመጣ እንደሆነ የመንገደኛው ዕቃ የሚስተናገደው በጭነት ማጓጓዣ ወደ አገር ውስጥ የመጣ ዕቃ በሚስተናገድበት የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ይሆናል፡፡<br>4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም የመንገደኛው ዕቃ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በጭነት ማጓጓዣ ወደ አገር ውስጥ የገባ እንደሆነ ዕቃው እንደ መንገደኛ ዕቃ ተቆጥሮ የመንገደኛ እቃ በሚስተናገድበት የጉምሩክ ስነ ስርአት መሠረት ይስተናገዳል፡፡ | • ተመላላሽ መንገደኛ የንግድ መጠን ያላቸውን ዕቃዎች በካርጎ ጭኖ የሚያመጣበት ሁኔታ በመኖሩ የንግድ ማጭበርበርን ለመከላከል፣ አዲስ የተጨመረ ንዑስ አንቀጽ<br><br>የመንገደኛው ዕቃ በየብስ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 5) ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በዉጭ አገር የሚኖሩ ዜጎች በሚኖሩበት አገር በተፈጠረ አስገዳጅ ሁኔታ ነዉ፡፡ | በበጭነት ማጓጓዣ ወደ አገር ውስጥ የመጣ ቢሆንም የመንገደኛው ዕቃ በሚስተናገድበት የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ይሆናል፡፡ |
| 10 | 33(2) | መንገደኞች የግል መገልገያዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ አገር ውስጥ ይዘው ለመግባት ወይም ወደ ውጭ ይዘው ለመውጣት ይፈቀድላቸዋል | 2) መንገደኞች የግል መገለልገያዎችን ከቀረጥ ነጻ ሆነው ወደ አገር ውስጥ ይዘው ለመግባት ወይም ወደ ውጪ ይዘው ለመውጣት የሚፈቀድላቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡ | የግል መገለልገያዎችን ከቀረጥ ነጻ ለማስገባት ወይም ለማስወጣት በገንዘብ ሚኔስቴር መመሪያ ይወሰናል፤ |
| 11 | 40(2) | ባለሥልጣኑ ለጉምሩክ ቁጥጥር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በውጭ አገር በአግባቡ የተመዘገበ የንግድ አገልግሎት ማጓጓዣ በጊዜያዊነት እንዲገባ ሲፈቅድ ዋስትና እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ | 2) የውጭ አገር የንግድ ማጓጓዣ ወደ አገር ውስጥ በጊዜያዊነት ሊገባ የሚችለው ማጓጓዣው በተመዘገበበት አገርና በኢትዮጵያ መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት ወይም የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሲፈቅድ ብቻ ይሆናል፡፡ | • እስካሁን ባለው ሁኔታ ለንግድ አገልግሎት ወደ ኢትዮጵያ ገቢ ዕቃዎችን ጭኖ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ዋስትና ተጠይቆ ስለማያውቁ፣<br>• ከሀገራችን ወደ ውጭ ጭነው የሚወጡ የሀገራችን ተሽከርካሪዎችም በጎረቤት ሀገሮች ዋስትና የማይጠየቁ በመሆኑ፣<br>• ዋስትና ይጠየቁ ቢባሉም ጎረበት ሀገሮች ተመሳሳይ ሕግን አውጥተው በተግባር ላይ ቢያውሉት ሀገሪቷ የራሷ ወደብ ስለሌላት ችግር ውስጥ የሚተገባ በመሆኑ፣ |
| 12 | 40 | | 5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ወደ አገር ውስጥ የገባ የውጭ አገር የንግድ ማጓጓዣ በአገር ውስጥ ጭነትና በወጪ ዕቃ ትራንስፖርት አገልግሎት መሰማራት አይችልም፣<br>6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ቢኖርም የትራንስፖርት ሚኒስቴር አገር ውስጥ የገባ የውጪ አገር የንግድ ማጓጓዣ ህጋዊ የወጪ ዕቃ ጭኖ ከአገር እንዲወጣ ሊፈቅድ ይችላል፡፡<br>7) በጊዜያዊነት ወደ  አገር ውስጥ  የገባ የውጭ አገር የንግድ መጓጓዣ በተወሰነለት ጊዜ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ ወይም በአገር ውስጥ ጭነትና በወጪ ዕቃ ትራንስፖርት አገልግሎት ተሰማርቶ የተገኘ እንደሆነ ብር 50 ሺህ ቅጣት ከፍሎ ማጓጓዣው ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ | • ተሽከርካሪዎቹ በሀገሪቷ ህግ ያልተመዘገቡ በመሆኑ ሀገር ውስጥ ሰርተው በሚያገኙት ገቢ ላይ ግብር ስለማይከፍሉ ሀገር ውስጥ አገልግሎት እንዳይሰጡ መከልከል አስፈላጊ መሆኑ፣<br>• ሀገር ውስጥ የሚቆዩበትን ጊዜ ኮሚሽኑ የመወሰን ስልጣን እንዲኖረው፣ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | • ሀገርቷን መጥቀሙ ከታመነበትና የወጪ እቃዎችን የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪ በመጥፋቱ ወጪ ዕቃ ወደ ውጭ በጊዜ መላክ በማይቻልበት ጊዜ በትራንስፖርት ባለሥልጣን ሁኔታው ከሀገር ጥቅም አንፃር ታይቶ የሚፈቀድበት ሁኔታ እንዲኖር ለማስቻል፤<br>• ያለፈቃድ ሀገር ውስጥ አገልግሎት ሲሰጡ ከተገኙ የሚወሰድባቸው እርምጃ ግልፅና ሊፈፀም የሚችል እንዲሆን ለማድረግ፤<br>• ቀደም ሲል የነበረው የቅጣት ሥርዓት በጎሮቤት ሀገራት መካከል ጭቅጭቅና ቅሬታ ከመፍጠር ያለፈ የሚፈፀም ስላልነበረ መቀየር አስፈልጓል |
| 13 | 51(1፣2፣5፣6፣ 8 እና 11) | 1) ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ ወደ ሀገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተከናውኖበት ከማከማቻ መውጣት አለበት፡፡<br>2)ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፡፡<br>5) በስህተት ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ የገባ የቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚ ድርጅት ዕቃ በአስራ ሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ወደ ጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን መተላለፍ አለበት፡፡<br>6) ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ከተከናወነበት በኋላ ከ7 የሥራ ቀናት በላይ በማከማቻው ሊቆይ አይችልም፡፡<br>8) በጭነት መግለጫው ወይም በሌላ የንግድ ሰነድ | 1) ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ወይም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተፈጽሞበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፡፡<br>2) ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአስር ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተፈጽሞበት ከማከማቻው መውጣት አለበት<br>5) ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን መግባት የነበረበት ዕቃ በስህተት ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ መጋዘን ገብቶ የተገኘ እንደሆን በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ወደ ጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን መተላለፍ አለበት፡፡<br>6) ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከተፈጸመበት በኋላ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ከመጋዘን መውጣት አለበት፡፡<br>8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ወደ መንግስት የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች ከመወገዳቸው በፊት የዕቃው ባለቤት ሊከፍል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችንና አስተዳደራዊ | • ነባሩ አዋጅ በጊዚያዊ ዕቃ ማከማቻ ውስጥ የአስመጪዎች ዕቃ ለ60 ቀናትና ከዛ በላይ እንዲቆዩ የሚፈቅድ በመሆኑ፤<br>• አስመጪዎች የዕቃቸው ማከማቻ አድርገው እንዲጠቀሙበት እድል ስለሚሰጥ፤<br>• የቆይታ ጊዜው አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ፤<br>• ዕቃዎች ቶሎ ቶሎ ከመጋዘን እንዳይወጡ እያደረገ በመሆኑ፤<br>• አስመጪዎች ዕቃቸውን ቶሎ እንዲወስዱ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የተገጁት እቃዎች በሙሉ ጊዜያዊ የጉምሩክ እቃ ማከማቻ የሚገቡ ከሆነ ባለስልጣኑ የሚጠይቀው ሰነድ የጭነት መግለጫውን ወይም የንግድ ሰነዱን ይሆናል | መቀጫውን በመክፈል ዕቃዎቹን በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ የመረከብ መብት ይኖረዋል::<br>11) ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ የተወሰኑ የጊዜ ገደቦችን በበቂ ምክንያት ሊያራዝም ይችላል:: | ለማድረግ፤<br>• ዕቃው ወደ መንግሥት መጋዘን እንዲዛወር ከተደረገ በኋላ አስመጪው የዕቃውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል እቃውን ለመረከብ ቢመጣ በመዘግየቱ የሚጣልበት ቅጣት ያላስቀመጠ በመሆኑ አስመጪዎች ባሻቸው ጊዜ መጥተው እቃቸውን እንዲጠይቁ እያደረገ መሆኑ |
| 14 | 51(11) | | 12) የዚህ አንቀጽ (7) ድንጋጌ ቢኖርም ዕቃውን መልሶ ከአገር ለማስወጣት ጥያቄ ያቀረበ አስመጪ በአዋጁ የተወሰነውን 5 በመቶ ቀረጥና ታክስ በመክፈል ዕቃውን ከአገር መልሶ ማስወጣት ይቻላል:: | አዲስ የተጨመረ |
| 15 | 59(3) | 3) በዋስትና ሊለቀቁ የማይችሉ የተያዙ ዕቃዎች ባለቤቱ እንዲወስዳቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔው እስከተሰጠበት ቀን ድረስ በመጋዘን ለቆዩት ጊዜ የመጋዘን ኪራይ አይከፈልባቸውም:: በዚህ አይነት ባለቤቱ እንዲወስዳቸው የመጨረሻ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተፈፅሞባቸው ከመጋዘን መውጣት አለባቸው፡ | 3) የቀረጥና ታክስ ክርክር የተነሳባቸው በዋስትና የማይለቀቁ ዕቃዎች ወደ መንግስት የጉምሩክ መጋዘን መዛወር አለባቸው :: ሆኖም በህግ ክርክር ዕቃዎቹን ለባለቤቱ የተወሰነ እንደሆነ ክርክር ከተነሳበት ቀን ጀምሮ የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ለኮሚሽኑ እስከደረሰበት ቀን ድረስ ዕቃዎቹ በመጋዘን ለቆዩበት ጊዜ መክፈል ያለበት የመጋዘን ኪራይ በኮሚሽኑ ይሸፈናል:: | • ጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ባለመሆኑ ዕቃው የሌላ ድርጅት መጋዘን ውስጥ በነፃ እንዲቆይ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ፤<br>• በህግ ክርክር ምክንያት ዕቃዎች በመጋዘን ቆይተው ኮሚሽኑ ከተሸነፈ የመጋዘኑን ኪራይ መክፈል ስለሚጠበቅበት፤ የተያዙ ዕቃዎች ባለቤቱ እንዲወስዳቸው ከተወሰነ በኋላ የመንግሥት መጋዘን ውስጥ ለሁለት ወር እንዲቆዩ መፍቀድ አግባብ ባለመሆኑ |
| 16 | 67(1) | 1) የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው እንዲመለሱ በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ አይከፈልባቸውም:: ሆኖም የጥገና ወይም የማካካሻ ምርቶቹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 66 (3) መሠረት ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ ካልገቡ በዕቃዎቹ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከሚወሰን ቅጣት ጋር የሚከፈል ይሆናል:: | 1) የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው እንዲመለሱ በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ አይከፈልባቸውም:: ሆኖም የማካካሻ ምርቶቹ በዚህ በአዋጁ አንቀጽ 66(3) መሰረት ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ ካልገቡ በእቃዎቹ ላይ የሚፈለገው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይከፈልባቸዋል:: | • በተጨማሪም አስተዳደራዊ ቅጣቱን በግልፅ በአዋጁ ላይ ማስቀመጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 17 | 71(2) | 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ውጪ እቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡባቸው ሌሎች ሁኔታዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል | 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተመለከቱት ውጪ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡባቸው ሌሎች ሁኔታዎች የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል:: | በመጀመሪያው ላይ ሚኒስቴሩ የሚለው የገቢዎች ሚኒስተር ሣይሆን የገንዘብ ሚኒስቴር መሆኑን ለመግለፅ ነው፤ |
| 18 | 73(5፣6) | 5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ዕቃው አገር ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ ተደርጎ በዕቃው ላይ ተገቢው የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖበት አገር ውስጥ ሊቀር ወይም ሊወጣ ይችላል::<br>6) በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ከመንግስት አካላት ውጪ በሆነ ማንኛውም ሰው በቀረበ ክስ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በመያዙ ምክንያት ተመልሶ ሊወጣ ካልቻለ ተመልሶ የሚወጣበት የጊዜ መጠን ይቋረጣል:: | 5) በአዋጁ አንቀጽ 73(4) መሰረት ዕቃው አገር ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በሕግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ከአገር መውጣት አለበት:: ሆኖም ዕቃው ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ በእርጅና ቅናሹ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ እንዲሁም አስተዳደራዊ መቀጫ ሊከፈል የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ተደርጎ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል::<br>6) ማንኛውም ቱሪስት ተሸከርካሪን ጨምሮ የያዘውን የግል መገልገያ ዕቃ፣ በዋስትና በማስመዝገብ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ ሊገባ ይችላል:: ለዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም ሚኒስቴሩ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል:: | • አሁን ባለው አሠራርም የቱርስት ለቱርስት መኪና የሚያዝ ዋስትና በመኖሩ፣<br>• የተያዘ ዋስትና ዕቃው ስለሚሆን ገቢ ለማድረግ አስቸጋሪ ስለሚሆን (ተገቢው የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከነውኖበት ከሀገር ሊወጣ ወይም ሊቀር ይችላል የሚለው አወዘገቢ በመሆኑ ቀርቷል<br>• የግል መገልገያ ዕቃ፣ ቱሪስት ተሽከርካሪን በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ዋስትናው ራሱ ይሆናል፤ |
| 19 | 73 | | 7) ወደ አገር ውስጥ የገባ ቱሪስት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካልገጠመው ወይም የመቆያ ጊዜው ካልተራዘመለት በስተቀር በአዋጁ አንቀጽ 73 (1) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ማውጣት ያለበት ሲሆን ዕቃውን ከአገር ያላስወጣ እንደሆነ ዕቃው ውርስ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል::<br>8) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 አፈጻጸም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት አግባብነት ባለው ማስረጃ የሚረጋገጥ ከባድ ህመም ወይም በህግ ቁጥጥር ሥር መዋል ወይም ከአገር እንዳይወጣ መታገድ ወይም የእቃው መጥፋት ወይም መጎዳት እና ከነዚህ ጋር ተመሣሣይ የሆነ ቱሪስቱ እንዳይመለስ የሚያደርግ ማንኛውም አስገዳጅ ሁኔታ ማለት ነው::<br>9) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ቱሪስቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ፈቃድ ያገኘ እንደሆነ ወደ አገር ውስጥ ያስገባው ዕቃ የመኖሪያ ፈቃድ በተገኘበት ቀን ወደ አገር ውስጥ እንደገባ ተቆጥሮ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በመፈጸም ቀረጥና ታክስ ከፍሎ ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቀር ሊፈቀድለት ይችላል::<br>10) በጊዜያዊነት ዕቃ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ሰው ዕቃውን ከአገር ለማስወጣት የማይችልበት በቂ ምክንያት ካቀረበ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በመፈጸም በዕቃው ላይ ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቀር ሊፈቀደለት ይችላል:: | አዲስ የተጨመሩ ንዑስ አንቀጾች<br>• ዕቃው ውርስ መደረጉን፣ (ከአቅም በላይ ) ማለት ህመም፣በህግ ቁጥጥር ሥር መዋል፣ከአገር እንዳይወጣ መታገድ፣የእቃው መጥፋት ወይም መጎዳት፣ተመሳሳይሽ ማንኛውም አስገዳጅ ሁኔታ ነው፤<br>• የመኖሪያ ፈቃድ ሲያገኝ በተፈቀደለት ቀን ወደ ሀገር ውስጥ እንደገበ ተቆጥሮ ቀረጥና ታክስ ይከፍልል<br>• ዕቃውን ከአገር ለማስወጣት እንደማይችል በቂ ምክንያት ካቀረበ<br>• የተፈቀደለት መቅያ ጊዜ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 11) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 የተመለከተው ቢኖርም ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቀር የቀረበው ጥያቄ ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቆይ የተፈቀደለት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ከሆነ በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ አስመጪው ያስያዘው ዋስትና ተመላሽ ተደርጎ የቀረጥና ታክሱን 25 በመቶ መቀጫ ከፍሎ ዕቃው አገር ውስጥ እንዲቀር ይደረጋል፡፡<br>12) በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ በዚህ አንቀጽ መሠረት ተመልሶ ከአገር ያልወጣ ወይም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞበት አገር ውስጥ እንዲቀር ያልተፈቀደለት እንደሆነ ዕቃው ይወረሳል፡፡<br>13) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ቱሪስት" ማለት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመቆየት ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የውጪ አገር ዜጋ ሲሆን ለሥራ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባን ሰው  አይጨምርም፡፡ | ከተጠናቀቀ በኋላ ከሆነ የቀረጥና ታክሱን ሃያ አምስት በመቶ መቀጫ ከፍሎ እንደሚቀር<br>• እነውዲቀር ልተፈቀደ ከሀገር ያልወጣ እንደሆነ ዕቃው ይወረሳል<br>• "ቱሪስት" ማለት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ የውጪ አገር ዜጋ ነው፤ |
| 20 | 74 | ሚኒስቴሩ በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነጻ ሊሆን ስለሚችሉበት ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡ | የገንዘብ ሚኒስቴር በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ እቃዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከቀረጥ ነፃ ሊሆኑ ስለሚችሉበት ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡ | ሚኒስቴሩ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር መሆኑን |
| 21 | 75 | 1) በሚከተሉት ምክንያቶች በጊዜያዊነት ለመውጣት የጉምሩክ ፎርማሊቲ የተከናወነባቸው ዕቃዎች ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ተመልሰው መግባት ይችላሉ<br>ሀ) ወደ ውጪአገር ለሥራ የሄዱ ሰው የሄደበትን ሥራ ለማከናወን የተጠቀመባቸው ተሽከርካሪዎች፣ መሣሪያዎች<br>ለ) ለንግድ ለባህል፣ ወይም ለማናቸውም ዓይነት ትርዒት ወይም ኤግዚቢሽኖች ወደ ውጪ አገር የሚላኩ ዕቃዎች<br>2) በሚኒስቴሩ በወጣ መመሪያ በሌላ አኳኋን ካልሆነ በስተቀር ዕቃዎቹ በጊዜያዊነት ወደ ውጭ አገር ወጥተው ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው መግባት የማይችሉት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው የመጡ እንደሆነ ነው፡፡ | 1) የሚከተሉት ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው በጊዜያዊነት ከአገር ከወጡ በኋላ ቀረጥና ታክስ ሳይከፍልባቸው ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ  ይችላሉ፡፡<br>ሀ) ወደ ውጭ አገር ለሥራ ወይም ለጉብኝት የሄደ ሰው የሄደበትን ሥራ ለማከናወን የሚጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች፣ መሣሪያዎችና ማሽነሪዎች፡<br>ለ) ለንግድ ማስታዋወቅና ለባህል ልውውጥ ወይም ለማናቸውም ዓይነት<br>ትርዒት ወይም ኤግዚቢሽን ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች፣<br>ሐ) በፕሮጀክት ስምምነት መሰረት ለሥራ ወደ ውጭ የሚወጡ ዕቃዎች፣<br>2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት  በጊዜያዊነት ከአገር የወጡ ዕቃዎች<br>የሄዱበትን ዓላማ አጠናቀው ወደ አገር ውስጥ ሲመለሱ ቀረጥና ታክስ የማይከፈልባቸው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ የገቡ<br>እንደሆነ ብቻ ነው፡፡<br>3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም በፕሮጀክት ስምምነት  ለሥራ ወደ ውጭ አገር ወጥተው የሚመለሱ ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ የሚከፈልባቸው በፕሮጀክት ስምምነቱ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ገደብ ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ ያልገቡ እንደሆነ | • አዲስ የተጨመሩ፤ ለጉብኝት፣በፕሮጀክት ስምምነት በጊዜያዊነት የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎች የቀረጥና ታክስ ክፊያ በፕሮጀክቱ ስምምነት ጊዜ መሆኑ የሚወጡ የሚለው አዲስ የተጨመረ ሲሆን ሌለው የነበረ ነው፤ ኮሚሽኑ በቂ ምክንያት ጊዜውን ሊያረዝም እንደሚችል፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ብቻ ነው:: <br> 4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ በቂ ምክንያት ሲቀርብለት ዕቃዎች ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበትን ጊዜ ሊያራዝም ይችላል:: | |
| 22 | 76(1) | ለአገር ውስጥ ፍጆታ ተብሎ የተመዘገበ ዕቃ ያልተከለከለ ወይም አገባቡ የጉምሩክ ሕግን የማይፃረር ከሆነ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከመከናወኑ በፊት ወደ ውጭ አገር ተመልሶ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ 5% ተከፍሎበት እንዲወጣ ሊፈቀድ ይችላል:: | 1) ለአገር ውስጥ ፍጆታ ተብሎ ወደ አገር የገባ ዕቃ ያልተከለከለ ወይም አገባቡ የጉምሩክ ሕግን የማይፃረር ከሆነ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከመከናወኑ በፊት ወይም ከተከናወነ በኋላ ዕቃው ለነፃ ዝውውር ከመለቀቁ በፊት ወደ ውጭ አገር ተመልሶ እንዲወጣ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ 5% ተከፍሎበት እንዲወጣ ሊፈቀድ ይችላል:: | • ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ከተፈፀመበት በኋላ ቀረጥ በዝቶበት ወይም በሌላ ምክንያት መልሶ ለማውጣት ፈልጎ ጥያቄ ቢያቀርብ መፍቀድ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት |
| 23 | 90(1) | ወደ አገር ውስጥ የሚገባ ዕቃ የግብይት ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ለተሸጠው ዕቃ በትክክል የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ዋጋ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 96 የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች የታከሉበት ይሆናል:: | 1) በአዋጁ አንቀጽ 90(1) ላይ አንቀጽ 97 የሚለው ተሰርዞ አንቀጽ 96 በሚል ተስተካክሏል | • የትየባ ችግር ስለነበረው ብቻ ነው የተሻሻለው 97 የሚለውን በ96 ለመተካት ነው <br> • የዕቃዎች የስሪት አገር አወሳሰን <br> • |
| 24 | 104 | | 5) ኮሚሽኑ አስገዳጅ ለኤክስፖርት እቃዎች የስሪት አገር መረጃ ሊሰጥ ይችላል:: | • አዲስ 24/ በአዋጁ አንቀጽ 104 ከንዑስ አንቀጽ (4) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ (5) ተጨምሯል:: <br> • (5) ኮሚሽኑ አስገዳጅ የስሪት አገር መረጃ ሊሰጥ ይችላል:: |
| 25 | 117(4) | የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው ወደ ውጭ ለመላክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ ዕቃዎች የተገኙ ማካካሻ ምርቶች ወደ ውጭ መላካቸውን ወይም ካልተላኩ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን ለማረጋገጥ | 4 ) በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት የሚሸፈኑ ዕቃዎችን ሳይጨምር የምርት ወይም የጥገና ሂደታቸውን አጠናቀው ወደ ውጭ ለመላክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ ዕቃዎች የተገኙ ማካካሻ ምርቶች ወደ ውጭ መላካቸውን ወይም ካልተላኩ ቀረጥና ታክሱ መከፈሉን ለማረጋገጥ፤ | • በወጭ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት የሚሸፈኑ ዕቃዎች በሌላ አዋጅ የሚሸፈኑ ቢሆንም በነባሩ አዋጅ እዚህ በጥቅል በመጠቀሱ አንድ ላይ የሚታይበት ሁኔታ ስለነበረ ግልፅ ለማድረግ ታስቦ ነው የተሻሻለው፤ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 26 | 119(5) | ዋስትና ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ክፍያውን ሳይፈጽም ከቀረ ባለሥልጣኑ በገቢ ግብር አዋጁ በተመለከተው ሥነ-ሥርዓት መሠረት የባለእዳውን ወይም የዋስትና ሰጪውን ንብረት በመያዝ ክፍያው እንዲፈጸም ሊያደርግ ይችላል፡፡ | 5) ዋስትና ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ክፍያውን ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ኮሚሽኑ በታክስ አስተዳደር አዋጁ በተመለከተው ሥነ- ሥርዓት መሠረት የባለእዳውን ወይም የዋስትና ሰጪውን ንብረት ወይም የባንክ ሂሳብ በመያዝ ክፍያው እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ | • የአዋጁ ድንጋጌ በኮሚሽኑና በዋስትና ሰጪዎች መካከል አለመግባባትን እየፈጠረ በመሆኑ፣<br>• የገቢ ግብር አዋጅ የሚለውን በታክስ አስተዳደር አዋጅ ለመተካት፣<br>• በሰርኩላርም አሰራር የተዘረጋለት ስለሆነ ጥያቄውን በአዋጁ ለመመለስ፣ |
| 27 | 122(6) | 6) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተጠየቀውን ቀረጥና ታክስ ከመቀጫና ወለዱ ያልከፈለ ባለዕዳ በሥራ ላይ ባለው የገቢ ግብር አዋጅ የተመለከተው ንብረት ይዞ የማስፈጸም ሥርዓት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡ | 6) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተጠየቀውን ቀረጥና ታክስ ከነመቀጫና ወለዱ ያልከፈለ ባለዕዳ በሥራ ላይ ባለው የታክስ አስተዳደር አዋጅ የተመለከተው ንብረትን ይዞ የማስፈጸም ሥርዓት ተፈጻሚ ይሆንበታል፡፡ | • የገቢ ግብር አዋጅ የሚለውን በታክስ አስተዳደር አዋጅ ለመተካት፣ |
| 28 | 122 | | 7) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሙብት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን በሚመለከት ኮሚሽኑ የጉምሩክ ማጭበርበር የተፈጸመ መሆኑን ያመነ እንደሆነ በአምስት ዓመት ጊዜ ሳይገደብ ኦዲት ማድረግ ይችላል፡፡ | • ኮሚሽኑ በበቂ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ንግድ ማጭበርበር መኖር ሲያምን በጊዜ ወይም በደርጋ ሳይገደብ ኦዲት ማድረግ እንዲችል ለማድረግ ነው፣ |
| 29 | 123(2) | 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሊታይ የሚችለው ዕቃው የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናውኖበት ወደ አገር ከገባበት ወይም ወደ ውጭ አገር ከተላከበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከቀረበ ነው፡፡ | 2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሊታይ የሚችለው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተከናውኖበት ዲክላራሲዮን ከተበተነ ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከቀረበ ብቻ ነው፡፡ | • የጉምሩክ ፎርማሊቲ ተከናወነ የሚባለው መቼ እንደሆነ በትክክል የማይታወቅ በመሆኑ አስመጪው ወይም ላኪው ከጉምሩክ ዕቃ ከተለቀቀለት ቀን ጀምሮ አላቀረበም እየተባለ ተመላሽ የሚከለከልበት ሁኔታ በመኖሩ ግልፅ ማድረግ በማስፈለጉ ነው፡፡ |
| 30 | 124 | | ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ያልተከለከለ ወይም አገባቡ የጉምሩክ ህግን የማይጻረር መሆኑ ሲረጋገጥና አስመጪው ዕቃውን | • አስመጪው ያስገባው ዕቃን እንደማይፈልገው ገልጾ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | እንደማይወሰደው በጽሑፍ ሲያረጋግጥ አስቀድሞ ለዕቃው የከፈለው ቀረጥና ታክስ ተመለሽ እንዲደረግለት የጠየቀ እንደሆነ ዲክላራሲዮኑ ተሰርዞ ለዕቃው የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ተደርጎ ዕቃው እንዲወገድ ይደረጋል፡፡ | አስቀድሞ በዕቃው ላይ የከፈለው ቀረጥና ታክስ እንዲመለስለት ከጠየቀ ማስተናገድ እንዲቻል፣<br>• 93 ተጨምሯል ማለቱ በስህተት ነው |
| 31 | 125 | | 4) ገደብ የተደረገበት ዕቃ በሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል ወደ አገር እንዲገባ ባልተፈቀደ ጊዜ አስቀድሞ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ይደረጋል፡፡ | • ዕቃው አገር ውስጥ ከገባ በኋላ በተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ዕቃው የጥራት ደረጃውን ስለማያሟላ ተመልሶ ከአገር ይውጣ ወደ አገር እንዳይገባ በማለት ከጉምሩክ ከመለቀቁ በፊት ውሳኔ በመስጠት በዚህ አዋጅ መሠረት አስመጪው የቀረጥና ታክሱን 5 በመቶ ከፍሎ መልሶ ከአገር ባስወጣው እቃ ላይ አስቀድሞ የተከፈለው ቀረጥና ታክስን መመለስ እንዲቻል፣ |
| 32 | 129 | የገቢና ወጪ ዕቃዎችን በሚመለከት የቀረጥ ነፃ መብት በህግ፣ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡ | 1) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የቀረጥ ነጻ መብት የሚሰጠው የገንዘብ ሚኒስቴር ብቻ ይሆናል፡፡<br>2) ከዲፕሎማሲ ግንኙነት ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ በፈረመችባቸው እና ተቀብላ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የሚሰጡ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብቶች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እየተረጋገጠ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡<br>3) የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት እንዲፈቅዱ በህግ ለሌሎች የመንግስት አካላት የተሰጠው ስልጣን ለገንዘብ ሚኒስቴር ተላልፏል፡፡<br>4) ማንኛውም የመንግስት አካል በሚዋዋለው የፕሮጀክት ስምምነት መሠረት የሚፈቀድ የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ተፈፃሚ የሚሆነው በገንዘብ ሚኒስቴር ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል<br>5) ኮሚሽኑ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው መረጃ ይይዛል፣ ይከታተላል፤ እርምጃ ይወስዳል<br>6) የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ስለሚፈቀድበት ሁኔታና ስለአፈጻጸሙ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል | • የቀረጥና ታክስ ነፃ አሠጣጥ መብት በየመ/ቤቱ ተበታትኖ የሚሰጥ በመሆኑ ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ተሰባስቦ እንዲሰጥ ለማድረግ<br>• የገንዘብ ሚኒስቴር፣በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር<br>• ኮሚሽኑ ከቀረጥና ታክስ ነፃን መቆጣጠሩን<br>• ደንብ እንደሚወጣ<br>• ኮሚሽኑ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደ አገር የሚገቡትን ዕቃዎች ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው ለመቆጣጠር እንዲያስችለው |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 33 | 143(1) | | በአዋጁ አንቀጽ 143 ከንዑስ አንቀጽ (1) የሚከተለው ፊደል (ሐ) ተጨምሯል፡፡<br>ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል (ሀ) ከተመለከተው የተለየ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚወሰንባቸው ከሆነ ቅጣቱ እስከሚከፈል ወይም በቂ ዋስትና እስከሚቀርብ ድረስ | • አዲስ የተጨመረ፤ በአዋጁ አንቀጽ 147(1) ህገወጥ ጭነት ጭነው የሚያዙ ተሽከርካሪዎች አስተዳደራዊ ቅጣት እስከሚከፍሉ መያዝ እንደሚችሉ |
| 34 | 147(1) ሀ እና ለ) | ሀ) በኮንትሮባንድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ ዕቃዎች ወይም ቀረጥና ታክስ ሊከፈልባቸው የሚገባ ሆኖ በማናቸውም አኳኋን የተደበቁ ዕቃዎች፣<br>ለ) ተደብቆ የተገኘው ዕቃ ዋጋ በዲክለራሲዮን ከተመዘገበው አጠቃላይ ዋጋ 50 በመቶ በላይ ሆኖ ሲገኝ ተደብቀው የተገኙት ዕቃዎች | ሀ) በኮንትሮባንድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ወይም ወደ ውጪ የሚላኩ ዕቃዎች፣<br>ለ) መከፈል የነበረበት ቀረጥና ታክስ በህጋዊ ዕቃው ላይ መከፈል ከሚገባው ወይም  አስቀድሞ ከተከፈለው ጠቅላላ ቀረጥና ታክስ 50 በመቶ በላይ ሆኖ በህጋዊ ዕቃ ከለላነት ወደ አገር ውስጥ ሲገባ ወይም ከአገር ሲወጣ የተገኘ ዕቃ | • የተደበቁ ዕቃዎች፣ለሚለ ው ቢደበቁም ባይደበቁም<br>• መከፈል የነበረበት ቀረጥና ታክስ 50 በመቶ በላይ ሆኖ ሲገኝ፣ |
| 35 | 147 | ሰ) መቀጫ ተወሰኖበት በአዋጁ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መቀጫው ያልተከፈለበት ማጓጓዣ፤<br>ሸ) አገር ውስጥ እንዲቀር ያልተፈቀደለትና የቱሪስቱ የመቆያ ጊዜ በተጠናቀቀ በሰላሳ ቀን ውስጥ ተመልሶ ያልወጣ የቱሪስት ዕቃ | ሰ) መቀጫ ተወሰኖበት በአዋጁ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መቀጫው ያልተከፈለበት እና በአዋጁ አንቀጽ 147(1) ፊደል ተራ (ሐ) መሰረት ጥሪ ተደርጎለት ባለቤቱ ያልቀረበበት ማጓጓዣ<br>ሸ) አገር ውስጥ እንዲቀር ያልተፈቀደለት የቱሪስቱ ዕቃ የመቆያ ጊዜ . በተጠናቀቀ በሰላሳ ቀን ውስጥ ተመልሶ ያልወጣ እንደሆነ | አዲስ የተጨመሩ<br>• 147(1) ፊደል ተራ (ሐ) ፤በስህተት 143ንዑስ 4 ወይም 147ንዑስ 3ሐ ለማለት የትየባ ስህተት ነው |
| 36 | 147(3) ሀ እና ለ) | 3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወረሱ ዕቃዎችን ለማጓጓዝ በዋለ ማንኛውም ማጓጓዣ፡-<br>ሀ) ዕቃዎችን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ የተሠራ፣ የተለወጠ ወይም መደበቂያ አካል የተገጠመለት ከሆነ፣<br>ለ) የማጓጓዣው ባለቤት እያወቀ ድርጊቱን መፈጸም ለመከላከል ወይም ለማስቆም ተገቢውን እርምጃ ሳይወስድ ከቀረ፤ ወይም | ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 161 መሰረት መቀጫ የተወሰነበት የመጓጓዣ ባለቤት በአስተዳደራዊ መንገድ የተወሰነበትን የገንዘብ ቅጣት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ማጓጓዣውን ያልወሰደ እንደሆነ ማጓጓዣው ውርስ ተደርጎ እንዲወገድ ይደረጋል<br>ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው ማጓጓዣ እንስሳ ከሆነ ባለቤቱ መቀጫውን በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ እንስሳውን ያልተረከበ እንደሆነ ኮሚሽኑ እንስሳውን ወርሶ እንዲወገድ ይደረጋል | • በአስተዳደራዊ ቅጣት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ካልወሰደ ውርስ የደረጋል<br>• እንስሳ ከሆነ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ካልወሰደ ውርስ የደረጋል |
| 37 | 147(3) | | መ) ውርስ የሚደረግ ማጓጓዣ ባለቤቶች ከአንድ በላይ በሚሆኑበት ጊዜ ባለቤቶቹ ለመቀጫው የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል | አዲስ የተጨመረ ንዑስ አንቀጽ<br>• ውርስ የሚደረግ ማጓጓዣ ባለቤቶች የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት እንደለባቸው |
| 38 | 156 | | (4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተመልሶ እንዲወጣ የተወሰነበት ዕቃ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ የአስተዳደራዊ መቀጫው መከፈል እንደተጠበቀ ሆኖ ዕቃው ውርስ ተደርጎ ይወገዳል | • በህገዊ ዕቃ ከለላነት የሚገባ ዕቃ ላይ ያለን ክፍተት ለመዝጋት፣<br>• የህግ ገደብ ማድረግ በማስፈለጉ፣<br>• ህግን መተላለፍ ቅጣት የሚያስከትል እንዲሆን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ለማድረግ ነው<br>አዲስ የተጨመረ ንዑስ አንቀጽ |
| 39 | 157(1) እና (2) | 1) ማንኛውም ሰው ለጉምሩክ ፎርማሊቲ በቀረበ የዕቃ ዲክለራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ወይም አነስተኛ ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት ወደ አገር እንዲገባ ወይም እንዲወጣ ለማድረግ የሞከረ እንደሆነ ያልተከፈለው የዕቃው ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል<br>2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ጠቅላላ ከተከፈለው ቀረጥና ታክስ በብልጫ የሚፈለገው ከ10 በመቶ የማይበልጥ ከሆነ አስመጪው በልዩነት የተገኘውን ቀረጥና ታክስ ያለቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል:: | 1) ማንኛውም ሰው ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም በቀረበ የዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ ያልተመዘገበ ወይም ትክክለኛ መግለጫ ያልተሰጠበት ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት በህጋዊ ዕቃ ከለላነት ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ያደረገ ወይም የሞከረ እንደሆነ የተገኘው የቀረጥና ታክስ ልዩነት በዲክላራሲዮን በተመዘገበው ዕቃ ላይ መከፈል ከነበረበት ቀረጥና ታክስ ሃምሳ በመቶ የማይበልጥ ወይም ከሃምሳ በመቶ በላይ ሆኖ ከብር አንድ ሚሊዬን በታች መሆኑ ሲረጋገጥ ያልተከፈለው የዕቃው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በልዩነቱ ላይ ያልተከፈለው ቀረጥና ታክስ እጥፍ በሆነ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል::<br>2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በልዩነት የተገኘዉ ቀረጥና ታክስ መከፈል ከሚገባው ጠቅላላ ቀረጥና ታክስ ከ5 በመቶ የማይበልጥና ድርጊቱ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ጊዜ ብቻ የተፈፀመ እንደሆነ አስመጪው በልዩነት የተገኘውን ቀረጥና ታክስ ያለቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል | • በህጋዊ ዕቃ ከለላነት ወደ አገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ዕቃ ላይ ያለ ክፍተት ለመዝጋት፣<br>• በልዩነት ላይ የሚከፈል ቅጣት መሠረት ግልፅ ለማድረግ ነው<br>• የበልዩነት የሚገባ ዕቃ ወደ 5 በመቶ መቀነስና በአንድ ዓመት ጊዜ አንድ ጊዜ ብቻ እንዲሆን በመገደብ ያለውን ክፍተት ለመከላከል ነው፤፤<br>• የህጋዊ ንግዱ ፍትሐዊነት ለማስጠበቅ ነው |
| 40 | 157 | | 3) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖሩም ማንኛውም ሰው በዲክላራሲዮን ሳይመዘገብ በህጋዊ ዕቃ ከለላነት ወደ አገር ውስጥ ያስገባው ወይም ለማስገባት የሞከረው ዕቃ በአስመጪው የንግድ ፈቃድ የማይሸፈን ዕቃ የሆነ እንደሆነ አስመጪው የዕቃው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዕቃውን ዋጋ 100 ፐርሰንት መቀጫ ይከፈልበታል::<br>4) ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለበት ሞተር ወይም ሻንሲ የተገጠመለት ተሽከርካሪ ባለንብረት ሞተሩ ወይም ሻንሲው ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ወይም ከቀረጥ ነፃ የገባ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር በሞተሩና ወይም በሻንሲው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን እጥፍ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል::<br>5) የተሽከርካሪው ባለቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) በተወሰነው መሰረት የተሽከርካሪውን ቀረጥና ታክስ ከነመቀጫው በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ከፍሎ ያልተረከበ እንደሆነ ተሽከርካሪው ይወረሳል | • በስህተት 157(2) መሆን የነበረበት 154 ማለቱ<br>• የዘርፍ አስመጪነት ፈቃድ ሳይኖር ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች እንደ ኮንትሮባንድ ተቆጥረው የሚያስጠይቅ ለማድረግ ነው::<br>• በህገወጥ መንገድ የሚገባ ሞተር፣ ሻንሲ ገጥሞ የተገኘ ተሽከርካሪ ላይ ያለ የህግ ክፍተት ለመዝጋት<br>• ቀረጥና ታክስ እና ቅጣት ለመጣል የሚያስችል ድንጋጌ ነው::<br>• በህገወጥ መንገድ የሚገባ ሞተር ፣ሻንሲ ገጥሞ የተገኘ ተሽከርካሪ ላይ ያለ የህግ ክፍተት ለመዝጋት<br>• ቀረጥና ታክስ እና ቅጣት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ለመጣል የሚያስችል ድንጋጌ ነው፡፡<br>• በተወሰነ ጊዜ ገደብ ግዴታን በለመወጣት የወርስ እርምጃ ለመውሰድ በህግ ለመደንገግ ነው፡፡<br>አዲስ የተጨመረ ንዑስ አንቀጽ |
| 41 | 161 | በማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን ያላከበረ እንደሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 176(3) መሠረት በሚወጣ መመሪያ ላይ ተመሥርቶ ሊወሰድ የሚችል ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር 50,000 በማያንስና ከብር 100,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡ | 1) ማንኛውም አጓጓዥ<br>ሀ) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመንገደኞች ወይም የጭነት መግለጫ ካላቀረበ<br>ለ) ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲገባ ካደረገ ወይም<br>ሐ) ማጓጓዣው ከጉምሩክ ወደብ እንዲወጣ ከተወሰነ በኋላ ምክንያቱን ለጉምሩክ ሹም ሳያስረዳና ፈቃድ ሳያገኝ እንዲቆይ ካደረገ ከብር 2000 ባላነስ እና ከብር 5000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል<br>2) ማንኛውም አጓጓዥ ጉምሩክ ወደብ በደረሰ ማጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሹም በሌለበት ዕቃ የጫነ ያራገፈ ወይም ለመጫን ወይም ለማራገፍ ሙከራ ያደረገ እንደሆነ ከብር 7000 በማያንስና ከብር 10,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡<br>3) ማንኛውም የኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነ ማጓጓዣ ባለቤት በኮንትሮባንድ ወንጀል ተሳትፎ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ በወንጀል የሚጠየቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀሉ ተሳትፎ ቢኖረውም ባይኖረውም የኮንትሮባንድ ዕቃው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጫነውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ዋጋ አንድ መቶ ፐርሰንት ወይም ብር አንድ መቶ ሺህ ከሁለቱ አነስተኛውን የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል<br>4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ቢኖርም ሲጓጓዝ የተያዘው የኮንትሮባንድ ዕቃ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የማይወጣለት የሆነ እንደሆነ የማጓጓዣው ባለቤት ብር መቶ ሺህ (100,000) የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡<br>5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተው ማጓጓዣ እንስሳ ከሆነ ባለቤቱ የተጫነውን የኮንትሮባንድ ዕቃ ዋጋ አንድ መቶ ፐርሰንት ወይም የእንስሳውን ወቅታዊ ዋጋ የሚያክል የገንዘብ መቀጫ ከሁለቱ አነስተኛውን የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል<br>6) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የተመለከተው ቢኖርም በማንኛውም ሁኔታ በማጓጓዣው ባለቤት ላይ በሚጣለው መቀጫ ከማጓጓዣው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መብለጥ የለበትም<br>7) ማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ባለፈቃድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያላከበረ እንደሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 178(3) መሠረት | • አንቀጽ 160 ለመሻር አንቀጽ 161 ተሻረ ሆኖም የአንቀጽ 161 አዋጁ ድንጋጌ በመሻሪያው አንቀጽ 40(7) ላይ የተካተተ በመሆኑ የሚፈጥረው ችግር የለም አንቀጽ 160 በዚህኛውም የተደገመ ከመሆኑ ሌላ ምንም የቀረ ድንጋጌ የለውም፤<br>• የአጓጓዥ ግዴታ መቀጫ<br>• የኮንትሮባንድ ዕቃ የጫነ ማጓጓዣ ወይም እንስሳ ባለቤት የኮንትሮባንድ ዕቃ ዋጋ አንድ መቶ ፐርሰንት ወይም ብር አንድ መቶ ሺህ ከሁለቱ አነስተኛውን የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል<br>• የኮንትሮባንድ ዕቃ ዋጋ አንድ መቶ ፐርሰንት ወይም የእንስሳውን ወቅታዊ ዋጋ የሚያክል የገንዘብ መቀጫ ከሁለቱ አነስተኛውን የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል<br>• መቀጫው ከማጓጓዣው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መብለጥ የለበትም<br>• የኮንትሮባንድ ዕቃ ዋጋ የማይወጣለት የሆነ እንደሆነ የማጓጓዣው ባለቤት ብር መቶ ሺህ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በሚወጣ መመሪያ ላይ ተመሥርቶ ሊወሰድ የሚችል ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ሃምሳ ሺህ (50,000) በማያንስና ከብር መቶ ሺህ(100,000) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡<br>8) ወደ ጉምሩክ ቦንድ መጋዘን መግባት ያለበት ዕቃ ወደ ጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ገብቶ የተገኘ በሚሆንበት ጊዜ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ወደ ተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን ያልተላለፈ ዕቃ አስመጪ ብር ሦስት ሺህ መቀጫ ከፍሎ ዕቃውን ወደ ቦንድድ መጋዘን እንዲያስተላልፍ ወይም ዕቃው በጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ እያለ የጉምሩክ ስነ ስርዓት እንዲፈጸምበት ይደረጋል<br>9) የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት የተፈጸምበት ዕቃ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ከመጋዘኑ ያልወጣ እንደሆነ አስመጪው መቀጫ ከፍሎ ዕቃው ከመጋዘን እንዲወጣ የደረጋል<br>10) ወደ ጉምሩክ መጋዘን የገባ ዕቃ ከመወገዱ በፊት አስመጪው ዕቃውን መረከብ የሚፈልግ ከሆነ አስመጪው ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎች መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀረጥና ታክሱን 20 በመቶ የገንዘብ መቀጫ መክፈል አለበት<br>11) ወደ አገር ውስጥ በጊዜያዊነት የገባ ዕቃ በአዋጅ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ አስመጪው በእርጅና ቅናሹ ላይ የሚከፈለው ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎች መከፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህኑ ቀረጥና ታክስ 25 በመቶ መቀጫ ከፍሎ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ተደርጎለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል | (100,000) የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡<br>• ጉምሩክ ቦንድ መጋዘን መግባት ያለበት ዕቃ ወደ ጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ገብቶ የተገኘ በሚሆንበት ጊዜ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ወደ ተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን ያልተላለፈ ዕቃ አስመጪ ብር ሦስት ሺህመቀጫ ከፍሎ ዕቃውን ወደ ቦንድድ መጋዘን |
| 42 | 162 | ማንኛውም ሰው የጉምሩክ የትራንዚት ሥነሥርዓትን በሚመለከት ተፈጻሚነት የሚኖረውን የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያላከበረ እንደሆነ ከብር 5 ሺህ በማያንስና ከብር 20ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡ | 1) ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በጉምሩክ ደንብ ወይም ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተደነገገውን የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ ሥርዓት ያላከበረ እንደሆነ ከብር 5 ሺህ በማያንስና ከብር 20 ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡<br>2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ተላላፊ የትራንዚት ዕቃ የሚያጓጉዝ ማጓጓዣ በተወሰነለት ጊዜና መስመር ተጓጉዞ ከአገር መውጣቱ ያልተረጋገጠ እንደሆነ የተያዘው ዋስትና ለመንግስት ገቢ ይሆናል<br>3) ተላላፊ የትራንዚት ዕቃ የሚያጓጉዝ ማጓጓዣ ዕቃው ተራግፎ ወይም ተደብቆ የተገኘ እንደሆነ ዕቃው ይወረሳል<br>4) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ቢኖርም ዕቃው የዘገየው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በጉዞ ላይ እያለ መሆኑ ከተረጋገጠ የተያዘው ዋስትና ገንዘብ ተመላሽ ይደረጋል<br>5) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 አፈጻጸም "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት በማጓጓዣው ላይ የደረሰ ብልሽት ወይም አደጋ ወይም በአጓጓዡ ላይ የደረሰ ከባድ ህመም ወይም የመንገድ መዘጋት ወይም ከልከላ ወይም | • የትራንዚት ሥነ ሥርዓት ያለማክበር ራሱን ችሎ ቅጣት እንዲኖረው ለማድረግ ነው<br>• የየትራንዚት ሥነ ሥርዓት ያለማክበር ራሱን ችሎ ቅጣት እንዲኖረው ለማድረግ ነው<br>• ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት<br>• ብልሽት ወይም አደጋ<br>• ከባድ ህመም ወይም የመንገድ መዘጋት ወይም ከልከላ ወይም በፀጥታ<br>• ዕቃው ተራግፎ ወይም ተደብቆ የተገኘ በተወሰነለት ጊዜና መስመር የተጓዘ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 46 | 169 | | 3) የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ሳይኖረው የቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ያለው በማስመሰል በማንኛውም የተጭበረበረ ሁኔታ ቀረጥ ሳይከፈልበት ዕቃ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ ወይም ከአገር ያስወጣ ወይም ወደ አገር ለማስገባት ወይም ከአገር ለማስወጣት የሞከረ እንደሆነ ከሰባት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከብር 100ሺህ በማያንስና ከብር 200ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡<br>4) መከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ላለመከፈል ወይም ለማሳነስ በማሰብ፣<br>(ሀ) ማንኛውንም ሐሰተኛ ሰነድ ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ያቀረበ እንደሆነ፤<br>(ለ) ሐሰተኛ መረጃ ወይም መግለጫ ለጉምሩክ ያቀረበ እንደሆነ፤<br>(ሐ) ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚቀርቡ ሰነዶችን የሰረዘ፣ የደለዘ፣ የፋቀ ወይም  አስመስሎ የሰራ እንደሆነ ወይም፤<br>(መ) ሌሎች ማናቸውንም የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና በብር 200ሺህ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡ | አዲስ የተጨመረ ንዑስ አንቀጾች<br>• በማስመሰል ማጭበርበር ከሰባት ዓመት -አስር ዓመት በጽኑ እስራት እና ከብር 100ሺህ - ከብር 200ሺህ መቀጫ<br>• ሐሰተኛ ሰነድ፣ሐሰተኛ መረጃ ወይም መግለጫ፣ ሰነዶችን የሰረዘ፣ የደለዘ፣ የፋቀ ወይም  አስመስሎ የሰራ<br>• ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስር ዓመት<br>• 200ሺህ የገንዘብ መቀጫ |
| 47 | 180(2) | 2) ባለስልጣኑ  ይህን አዋጅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ፣ መሠረት የሚወጣ ደንብ  ማሻሻያ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ፡፡ | 2) ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡ | መመሪያ የማውጣት ስልጣን |
| 3 | 183 | ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጠበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ህዳር 30 /2007 | ይህ አዋጅ በፌዴራል በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጠበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል መስከረም 19 ቀን 2012 | መስከረም 19 ቀን 2012ዓ.ም |